NABU

PARTNERSHIP FOR LAKE TANA WATERSHED, ETHIOPIA

WATER FOR LIFE



በጣና ሐይቅ ተፋሰስ ውስጥ ያለው የቆሻሻ አስተዳዳር እና መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል



ቆሻሻዎችን በየዘርፋቸው የመለየት አስፈላጊነት

ሰዎች ስለአካባቢ ጥበቃ ሲወያዩ ቆሻሻ በጣም ቁልፉና ዋናው የመወያያ አጀንዳ እየሆነ መጥቷል። ምንም እንኳን ሙሉ በሙሉ ቆሻሻ እንዳይፈጠር ማድረግ የማይቻል ቢሆንም በባለሙያዎች የሚመከረው መፍትሄ ቆሻሻ ቤት ላይ ሲወጣ መቀነስና ወደ ዜሮ ማድረስ ነው። በሌላ በኩል ከቆሻሻ ጥቅም ሊሰጡ የሚችሉ የተለያዩ ነገሮችን ማምረት ወይንም ከቆሻሻ ሀይል ማመንጨት ሁለተኛው የማስወገጃ አማራጭ ነው። የተለያዩ ቆሻሻ አይነቶች በአንድ ላይ ከተደባለቁ ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል በጣም አስቸጋሪ ስለሚያደርገው ቆሻሻን ከምንጩ መለየት ጥቅም ላይ ማዋሉን ለማሳለጥ በጣም አስፈላጊና ተመራጭ ነው።

ቆሻሻን ከመንጩ መለየት ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ ከማዋሉ ባሻገር በአካባቢ ጥበቃ ላይ እና በሰዎች ጤና ላይ የሚኖረው ፈይዳ ከፍተኛ ነው። ሁሉም ቆሻሻ አይነቶች በቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ተደባለቀው የሚወገዱ ከሆነ ጎጂ ጋዞችን የማምረት እና ተፈጥሮ ሀብቶቻችንን የመበከል እድላቸው በጣም ከፍ ያለ ነው።

በቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ውስጥ ምን ምን ይጣላል?



ለሚበሰብሱ ቆሻሻዎች

ለምግብ ነክ ቆሻሻዎች፣ ለእንቁላል ቅርፊቶች፣ ለቡናና የሻይ አተላዎች/ተረፈ ምርቶች፣ የለውዝ ገለባዎች፣ የጓሮ እርሻ ተረፈ ምርት እና የሳር ቁርጥራጮች፣ ከቤት ግቢ ውስጥ የሚወጡ እፅዋት ቅጠሎች እና እንጨቶች፣ የጣውላ ቁርጥራጮች፣ ከጥጥ እና ከሱፍ የተሰሩ አሩጌ ጨርቆች እና ምድጃ አመድ

እባክዎን በዚህ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ ቀጥሎ የተገለፁትን ቆሻሻዎችን አይጣሉ፡ ስጋ፣ ዓሳ፣ እንቁላል ወይም የዶሮ ስጋ ተረፈ ምርትን፣ የወተት ተዋጽኦ፣ ከእንስሳት የሚገኝ ስብ፣ የተሸከርካሪ ቅባቶችና ዘይቶች፣ የድንጋይ ከሰል /የድንጋይ ከሰል አመድ፣ በበሽታ ወይም በነፍሳት የተጎዱ እፅዋት፣ ከቤት እንስሳት ጋር የተገናኘ ቆሻሻ፣በኬሚካሎች የተቀቡ የእርሻ ቦታ አጥሮች



የወረቀት ቆሻሻዎች

ንጹህ እና ደረቅ ወረቀቶች፣ ነጭ የቢሮ ወረቀቶች፣ ጋዜጣዎች፣ ባለቀለም የቢሮ ወረቀቶች፣ ካርቶን፣ ነጭ የኮምፒተር ወረቀቶች፣ መጽሔቶች፣ ካታሎጎች እና የስልክ ቁጥር ማውጫዎች በዚህ የቆሻሻ ማጠራቀሚ ቅርጫት ውስጥ የሚጣሉ ናቸው።

እባክዎን በዚህ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ ቀጥሎ የተገለፁትን ቆሻሻዎችን አይጣሉ፡- የተሸፈነ እና በኬሚካል የተቀቡ ወረቀቶች፣ ከምግብ ጋር የተነካኩ ወረቀቶችን፣ የጭማቂ እና የእህል መያጃ ካርቶኖችን፣ የወረቀት ኩባያዎችን፣ እንደ ፎጣ ለእጅ መጥረጊያነት የሚያገለግሉ ወረቀቶችን፣ በፕላስቲክ የታሸገ ወረቀቶችን ወይም መጽሔቶችን



ሌሎች ከቤት ውስጥ የሚወጡ ቆሻሻዎች

ከላይ ከተዘረዘሩት የቆሻሻ ምድቦች ውስጥ የማይካተቱት ሌሎች ቆሻሻዎች ሁሉ ደግሞ በሁለተኛው የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ ይጣላሉ።

እባክዎን በዚህ የቆሻሻ ማጠራቀሚ ቅርጫት ውስጥ የሚበሰብሱ ቆሻሻዎችንና የወረቀት ቆሻሻዎችን አይጣሉ።

ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል

ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል ማለት ወደ ቆሻሻ የተቀየረው ቁስ የተወሰኑ ሂደቶችን እንዲያልፍ ከተደረገ በኋላ ለማህበረሰቡ ጥቅም የሚሰጥ ምርት ለማምረት የሚያገለግሉ የፋብሪካ ጥሬ እቃ የማምረት ሂደት ነው። በመሆኑም ቆሻሻን እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል ማለት ቆሻሻ የተወሰኑ ሂደቶችን እንዲያልፍ በማደረግ እና በማከም ቆሻሻ ወደ ሀብትነት የመቀየሩ ሂደት ነው። እነዚህ በዘላቂነት አካባቢያዊ አውቀትን መሰረት ተደርጎ የሚሰሩ በመሆኑ በዚሁ አካባቢ ቆሻሻ እንደ ሀብት ምንጭነት ሆኖ ያገለግላሉ።

ከቆሻሻ ምን ምን ይዘጋጃል?

ኮምፖስትን ማዘጋጀት

የመበስበስ ባህሪ ያላቸው ቆሻሻዎች ሳይንሳዊ አሰራርን በመከተል እንዲበሰብሱ ከተደረጉ በኋላ ለተክሎች በማደበሪያነት በማገልግል ተክሎች/ሰብሎች ምርታማነታቸው እንዲጨምር ያደርጋሉ። ከቆሻሻ የተፈጥሮ ማደበሪያ በማምረት ቆሻሻን ጥቅም ላይ ማዋሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የኬሚካል ማደበሪያዎችን በመተካት ለሰው ልጆች ጤንነት መሻሻል ላይ ከፍተኛ አስተዋፆ ያደርጋል።.

አዲዲስ ወረቀቶች እና የእጅ ሥራዎች

ወረቀቶች ልክ እንደ ዛፎች ዋጋ አላቸው። ከየቤቱ እና ከየቢሮዎች የሚሰበሰበው ወረቀቶች የተለያዩ ሂደቶች በማለፍና እንደ አዲስ ቦርሳ፣ የማስታወሻ ደብተሮች ለማዘጋጀት ወዘተ ይዘጋጁበታል። በመሆኑም የአገለገሉ ወረቀቶች ሰብስቦ ጥቅም ላይ በማዋል በርካታ የገቢ ማስገኛ ተግባራትን ማከናውን የሚቻል ሲሆን በተለይም ለሴቶች የስራ አድል ለመፍጠር አስተዋፅያ የጎላ ነው።

የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ

በዚህ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት ውስጥ ያሉ ቆሻሻዎች በከተማ አስተዳዳሩ ቆሻሻ ማሰባሰብ ስርዓት ውስጥ ከገቡ በኋላ ወደ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ይወሰዳል ማለት ነው።



የፕላስቲክ ጠርሙሶች እና ሌሎች ቆሻሻዎች በየቦታው ማለትም ከመሃል ከተማ እሰከ ከተማ ዳርቻዎች ድረስ ወዳድቀው ይገኛሉ። እነዚህ ቆሻሻዎች ለተፈጥሮ ሀብቶቻችን፣ ለእንስሳት እና ለማህበረሰቡ ጤና ከፍተኛ ስጋት በመሆን ላይ ናቸው።



የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር በጥልቅ የተሳሰረ ነው። የተጠበቀ፣ ጤናማ እና ለህብረተሰቡ የተሟላ አገልግሎት የሚሰጥና ሥነ -ምህዳር ለእሁኑ ትውልድ ብቻ ሳይሆን ለቀጣይ ትውልድ የኑሮ ዋስትናም መሰረት ነው።

የረጅም ጊዜ ግብ

በአሁኑ ጊዜ ለሰው ልጆች ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉ ተፈጥሮ ሀብቶቻችን ሁሉ ከቁጥጥር ውጭ በሆኑበት ዓለም ውስጥ እየኖርን እንደሆነ ይታወቃል። በመሆኑም ዘላቂነት ያለውን ልማት ለማስፋፋት ለሁላችንም የሚቀርበው ጥሪ ግልፅ ነው፣ የተፈጥሮ ሀብቶቻችንን ከመራቆት ለመታደግ ከአሁን ሰዓት የተሻለ አማራጭ ጊዜ የሌለን በመሆኑ የአሁኑ ትውልድ ያሉንን የተፈጥሮ ሀብቶቻችን በአግባቡ ጠብቀን፣ ተንከባክብንና በአግባቡ ተጠቅመን ለቀጣዩ ትውልድ ማስረከብ ይኖርብናል።

እዚህ የቀረቡት ተግባራት ሁሉ የውሃ ለሕይወት ፕሮጀክት አካል ናቸው፣ ነገር ግን ከእዚህ የምናገኘው እውቀት ለአሁን ብቻ የሚገለግል ሳይሆኑ ለቀጣዩ ትውልድ ህልውናም ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ከዚህ ድርጊት በስተጀርባ ያለው ዋና ግብ ቆሻሻ ምን ያህል ዋጋ ሊኖረው እንደሚችል ለማሳየት እና የማይፈለግን ነገርን (ቆሻሻን) የገቢ ምንጭ በማደረግ እንዲሁም አካባቢያችን እንዲጠበቅ ማስቻል ነው።

በጋራ በመስራት የህዝብ ጤናን እና የኑሮ ደረጃን ማሻሻል፣ የተቀናጀ የስነምህዳር አገልግሎቶችን ለአሁንና ለወደፊት እንዲረጋገጥ ማስቻልን፣ የብዝሃ ሕይወት ጥበቃንና የመሳሰሉት ግቦችን ማሳካት እንችላለን። በመሆኑም ከቤተሰብ ጀምረን የተፈጥሮ ሀብቶቻችንን በመጠበቅ የጣና ተፋሰስን ከጉዳት እንታደግ!

www.en.nabu.de/water-for-life









NABU – The Nature and Biodiversity Conservation Union
Charitéstr. 3, 10117 Berlin, Germany
Tel. +49 (0) 30.28 49 84-0
Africaprogramme@NABU.de
www.en.NABU.de

Imprint

© 2021, The Nature and Biodiversity Conservation Union (NABU), Charitéstr. 3, 10117 Berlin, Germany. Text & Editing: Beatriz Waldmann, Sarah Stoll; Layout and Illustration: Sarah Stoll; Photos: inside: Philipp Schütz · back: 2nd from top right: Bruno D'Amicis, all others: Philipp Schütz.